በኢትዮጵያ ለልጆች ስለ ሕፃናት ከጥቃት ጥበቃ ማውራት ይፈልጋሉ?

እንግዲያውስ ይህ መመሪያ ለእርስዎ ነው!

ETHIOPIA HUB

UKaid from the British people

ማውጫ

ምህፃረ ቃላት ii

ከመጀመር የሚያስችሉ ጥቂት ነገሮች ! 1

ይህ የኪስ መመርያ ለማን ነው? 1

ይህን የኪስ መመሪያ መጠቀም ከመጀመርዎ
በፊት ሊኖርዎ የሚገቡ ነገሮች..................................2

ይህ የኪስ መመሪያ ለእርስዎ ምን
ሊያደርግልዎ ይችላል? 3

ይህ የኪስ መመሪያ ለምን ተዘጋጀ? 4

ይህን የኪስ መመሪያ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል 5

ስለ ልጆች ከጥቃት ጥበቃ ከልጆች ጋር
መነጋገር ለምን አስፈለገ? 6

ስለ ሕፃናት ከጥቃት ጥበቃ ከልጆች ጋር
ለመነጋገር ዋና መርሆዎች 9

ስለ ልጆች ከጥቃት ጥበቃ ከልጆች ጋር
እንዴት መነጋገር እንደሚቻል 11

የአንድ ድርጅት ጥቃትን ለመከላከል እና ምላሽ መስጠት
የድርጅቱን ቁርጠኝነት እንዴት መግለፅ እንደሚቻል 12

ለልጆች የጥቃትን ፍቺዎች እንዴት መግለፅ እንደሚቻል 13

ልጆች የጥቃት አደጋ እንደተጋረጠባቸው ከተሰማቸው
ማን ማድረግ እንዳለባቸው እንዴት ማውራት እንደሚቻል...15

የጥቃት ምልክቶችን እንዴት መለየት
እና ይፋ ማድረግ እንደሚቻል 21

መሣርያዎች እና መርጃዎች 26

ETHIOPIA HUB

ምህፃረ ቃላት

CBCM Community Based Complaints Mechanism ማኅበረሰብ ተኮር ቅሬታ ማቅረቢያ ዘዴ

CSO Civil Society Organisations የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች

GBV Gender Based Violence ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት

NGO Non-Governmental Organisation መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት

IASC Inter-Agency Standing Committee የኢንተር-ኤጀንሲ ቋሚ ኮሚቴ

PSEA Protection from Sexual Exploitation and Abuse ከወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት መጠበቅ

RSH Resource and Support Hub የመረጃ እና ድጋፍ ማዕከል

SEA Sexual Exploitation and Abuse ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት

SEAH Sexual Exploitation, Abuse and Harassment ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ

UNCRC United Nations Convention on the Rights of a Child የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስምምነት

ለመጀመር የሚያስችሉ ጥቂት ነገሮች !

ይህ የኪስ መመርያ ለማን ነው?

ከዚህ በታች ያሉት ነጥቦች እርስዎን/ ድርጅትዎን የሚመለከቱ ከሆነ ይህ መመሪያ ለእርስዎ ነው።

በኢትዮጵያ ያለው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅትዎ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅትዎ (መያድ) የሚተገብራቸው ፕሮግራሞች ወይም የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከልጆች ጋር ይገናኛሉ?

ሕጻናትን ጨምሮ ከማኅበረሰቡ አባላት ጋር ስለ ሚተገብራቸው ፕሮግራሞች እና በሚያቀርባቸው አገልግሎቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚችሉ የሚነጋገር የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሠራተኛ ነዎት?

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ከጥቃት ጥበቃ መረጃን ለልጆች ለሚጋሩ ሠራተኞች ሊያገለግል ይችላል። ለምሳሌ የማኅበረሰብ ተሳትፎ ሠራተኞች ፣ የጥበቃ የትኩረት ነጥብ ወይም የልጆች ጥበቃ ባለሙያዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ይህንን መመሪያ የሚጠቀሙ ከልጆች እና ከማኅበረሰቡ አባላት ጋር የሚሠሩ ሠራተኞች ሁሉ ከጥቃት ጥበቃ ሥልጠና መውሰዳቸው አስፈላጊ ነው።

ETHIOPIA HUB

ይህን የኪስ መመሪያ መጠቀም ከመጀመርዎ በፊት ሊኖርዎ የሚገቡ ነገሮች

ከመጀመርዎ በፊት በድርጅትዎ የሚከተሉትን መኖሩን ያረጋግጡ።

- የጥቃት ጥበቃ ወይም የወሲባዊ ብዝበዛ፤ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መከላከል ፖሊሲ
- የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊ
- ሁሉም የሚመለከታቸው ሠራተኞች የጥቃት ጥበቃ ሥልጠና ወስደዋል።
- ማኅበረሰብ ተኮር ቅሬታ ማቅረቢያ /ጥቆማ ማድረጊያ ዘዴዎች በሥራ ላይ ናቸው።
- በአካባቢው ያሉ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ልየታ (የአድራሻ ዝርዝሮችን ወዘተ ጨምሮ) እንዲሁም የሪፈራል ሰቅድ፤ ተጎጂዎችን / ከጥቃት የተረፉትን ወደ አገልግሎቶቹ መላክ ካስፈለገ
- ልጆችን ጨምሮ ከተጎጂዎች/ከጥቃት የተረፉት ጋር ከመሥራት የተዘገጀ አንድ/ ጥቂት የሰለጠኑ ሠራተኞች
- የሰለጠኑ የጥቃት ጥበቃ መርማሪዎች ዝርዝር/ መርማሪዎችን ማግኘት መቻል

ከላይ ያለውን ከመረዳት እና ከበለጠ መረጃ የኢትዮጵያ የጥቃት ጥበቃ መረጃ እና ድጋፍ ማዕከልን ወይም እኛን ለማግኘት እዚህ እዚህ ጠቅ ያድርጉ።

ይህ የኪስ መመሪያ ለእርስዎ ምን ሊያደርግልዎ ይችላል?

ይህ መመሪያ ከልጆች ጋር ስለ ልጆች ከጥቃት ጥበቃ እንዴት መነጋገር እንደሚቻል መረጃ እና መመሪያ ይሰጣል። በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የሲቪል ማኅበረሰብ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከጥቃት ጥበቃ ምን ማለት እንደሆነ እንዲሁም ከሠራተኞች[1] እና ከፕሮግራሞች ምን እንደሚጠበቅ ለልጆች ማስረዳት መቻላቸውን ማረጋገጥ እንፈልጋለን። ይህም ተገቢ የሆነና እና ተገቢ ያልሆነ የሠራተኞች ባህሪያት ምን እንደሚመስል እንዲሁም ልጆች በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የሲቪል ማኅበረሰብ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት በደል ወይም ጉዳት ካጋጠማቸው ወይም ካዩ እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚችሉ ያካትታል።

ይህ መመሪያ የሚያተኩረው ወሲባዊ ብዝበዛን ጨምሮ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በሠራተኞቻቸው[2] ስለሚደርስባቸው ጥቃት፣ ከልጆች ጋር በመነጋገር ላይ ነው። ስለ ፆታ-ተኮር ጥቃት (GBV) ወይም በአጠቃላይ በሕብረተሰቡ ውስጥ ባሉ ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ማውራትን አያካትትም።
ነገር ግን፣ ሁሉም ከልጆች ጋር የሚሠሩ የሲቪል ማኅበረሰብ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስለማንኛውም ዓይነት በደል (በማኅበረሰቡ ውስጥ በማንኛውም ሰው የሚደርስ ጥቃትን ጨምሮ) ከልጆች ሪፖርት የማቅረቢያ ሥርዓቶችና ከልጆች ሪፖርት የመቀበያ ዘዴ ሊኖራቸው ይገባል።

ይህ የኪስ መመሪያ የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን (ዩኤንሲአርሲ) የሕፃንፍቺን ይጠቀማል - ዕድሜው ከ 18 ዓመት በታች የሆነ ሰው። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እንደ የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን (ሲአርሲ) የአፍሪካ የሕጻናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተርን የመሣሠሉ ጠቃሚ ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ ሰነዶችን አፅድቋል። ከፀደቁት ስምምነቶች ጋር በማጣጣም አገሪቱ በተሻሻለው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ በሕጻናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን መቅጫ በዝርዝር አቅርባለች።

---

[1]ሠራተኛ ማለት ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት የሚሠራ (በቋሚ ወይም በጊዜያዊ)፣ በጎ ፍቃደኛ፣ ተቋራጭ፣ ተለማማጅ ሠራተኛ፣ ጎብኚ፣ የተቋራጭ ተቋራጭ ወዘተ
[2]ከላይ እንዳለው

ይህ የኪስ መመሪያ ለምን ተዘጋጀ?

በኢትዮጵያ ያሉ የሲቪል ማኅበረሰብ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሠራተኞች ስለ ጥቃት ጥበቃ በተለይ ወሲባዊ ጥቃትን የመሣሠሉ ጥንቃቄ የሚፈልጉ የጥቃት ጥበቃ ጉዳዮችን በተመለከተ ከልጆች ጋር መነጋገር እንደሚቸግራቸው ጠቁመዋል።

በደል የሚፈጸመው ተጎጂዋ/ው ወይም ከጥቃት የተረፈችው/የተረፈው በለበሱት ወይም ያሳዩት በነበረው ባህሪ ምክንያት አይደለም። ለአንድ ልጅ ትምህርትን 'ማስተማር' ስለሚያስፈልግ አይከሰትም። በደል የሚከሰተው በኃይል አለመመጣጠን እና ሠራተኞች በደልን/ጥቃትን ለመፈጸም የሚያስችላቸው መዋቅር ሲኖር ወይም በተገቢው ሁኔታ ያልታቀደ ፕሮግራም ወይም ግንኙነት ጉዳት ለማድረስ በሚያስችል መልኩ ሲቀረጽ ነው።

ለምሳሌ:

- የሲቪል ማኅበራት ሠራተኞች[3] ልጆቹን አላግባብ ሊያጠቁ ይችላሉ
- ልጆችን ጨምሮ ሌሎች የማኅበረሰብ አባላት በፕሮግራሙ ውስጥ ያሉ ልጆችን አላግባብ ሊያጠቁ ይችላሉ። ለምሳሌ ቤተሰቦች በማይመቻቸው እና ምላሽ ሊሰጡባቸው በማይችሉ ጉዳዮች ላይ ልጆች እንዲናገሩ ድጋፍ እየተደረገላቸው ነው፤ ልጆች በጋራ እንዲሳተፉ ይጠበቅባቸዋል፣ ነገር ግን በፕሮግራም እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሚሳተፉበት ጊዜ አንዳቸው ከሌላው ጋር እንዴት ምን ዓይነት ባህሪ ማሳየት እንዳለባቸው ድጋፍ አይደረግላቸውም።
- የማኅበረሰብ ወይም የቤተሰብ አባላት ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ግንኙነቶች ለተነሱ የጥቃት ጉዳዮች ምላሽ በመስጠት ልጅን ሊበድሉ/ ሊያጠቁ ይችላሉ።

[3]ሠራተኛ ማለት ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ላልሆነ ድርጅት የሚሠራ/የምትሠራ (በቋሚ ወይም በጊዜያዊ)፣ በጎ ፍቃደኛ፣ ተቋራጭ፣ ተለማማጅ ሠራተኛ፣ ኅብኚ፣ የተቋራጭ ተቋራጭ ወዘተ

ይህን የኪስ መመሪያ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል[4]

- **ለሕፃናት ማውራት አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?** ይህ ክፍል ልጆችን ስለጥቃት ጥበቃ የማውራት እና ዝግጁ መሆንዎን የማረጋገጥ ገጥ አስፈላጊነትን ያብራራል።

- **ከልጆች ጋር ስለ ልጆች ከጥቃት ጥበቃ ሲነጋገሩ የሚከተሏቸው ዋና ዋና መርሆች፡** ይህ ክፍል ከልጆች ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ መከተል ያለብዎን መርሆዎች ያካትትታል።

- **ስለ ልጆች ከጥቃት ጥበቃ ከልጆች ጋር እንዴት መነጋገር እንደሚቻል፡** ይህ ክፍል የሕፃናት ጥበቃን ከልጆች ጋር እንዴት እንደሚወያዩ መመሪያ ይሰጣል። መመሪያው ለልጆች የተለያዩ የጥቃት ዓይነቶችን በተገቢው ሁኔታ ሊያብራሩ የሚችሉበትን ቃላት ያካትታል እንዲሁም ድርጅቱ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ እያደረገ ያለውን ጥረት ለማስረዳትና እና ስጋቶቻቸውን ሪፖርት እንዲያደርጉ ለማበረታታት ያስችልዎታል።

- **የጥቃት ምልክቶችን እንዴት መለየት እና ይፋ ማድረግ፡** ይህ ክፍል ከልጆች ጋር የሚነጋገሩ ሰዎች የጥቃት ምልክቶችን እንዲለዩ ወይም ቅሬታን እንዲቀበሉ ይረዳል (ከልጆች ጋር ስለ ጥቃት ሲነጋገሩ ይህ የተለመደ ሊሆን ይችላል)።

መሳሪያዎች እና መርጃዎች (Tools and Resources) መጨረሻ ላይ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የሚችሉባቸውን አስፈላጊ ኃብቶች እና አገናኞችን ይዘረዝራል (አብዛኛዎቹ በእንግሊዝኛ ናቸው)።

[4] የኪስ መመሪያው በአማርኛ፣ በአፋን ኦሮሞ፣ በትግርኛ እና በሶማሊኛ ይገኛል። እነዚህ መመሪያዎች እንደ እንግሊዝኛው ተመሳሳይ ክፍሎች ይኖራቸዋል።

ስለ ልጆች ከጥቃት ጥበቃ ከልጆች ጋር መነጋገር ለምን አስፈለገ?

ትክክል እና ስህተት የሆነውን እንዲሁም ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምን እንደሚጠበቅ እንዲያውቁ ከልጆች ጋር ስለ ልጆች ጥቃት እና የልጆች ከጥቃት ጥበቃ መነጋገር አስፈላጊ ነው።

ልጆች እንዲረዱት (“ከዕድሜ ጋር የሚስማማ መረጃ”) ከዕድሜያቸው ተስማሚ የሆነ መረጃ ሊሰጣቸው ይገባል። የምናካፍላቸው መረጃ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦

- ጥቃት ማለት ምን ማለት ነው?
- ማንን ማናገር እንዳለባቸው
- ስጋቶችን ወይም ክስተቶችን እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚችሉ
- የድጋፍ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚችሉባቸው መንገዶች

ያስታውሱ!

የሕፃናትን ጥቃት የሚያካትት እያንዳንዱ ሁኔታ የተለየ ነው፤ እንዲሁም እያንዳንዱ ልጅ በተለየ መንገድ ምላሽ ይሰጣል። ድርጅትዎ የቅሬታ ሪፖርቶችን ለመቀበል ዝግጁ ካልሆነ በስተቀር ከልጆች ጋር መነጋገር አይጀምሩ፣ ለምሳሌ በቦታው ላይ የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴዎች አሉት?

ጥቃት ምን እንደሆነ እና ድርጅትዎ ልጆችን ከጥቃት ለመጠበቅ ምን እየሠራ እንደሆነ ካልተረዱ ሠራተኞች ልጆችን እንዲያነጋግሩ አይጠይቁ።

ETHIOPIA HUB

ብዙ አዋቂዎች ከልጆች ጋር ስለጥቃት እና ስለጉዳት ጉዳዮች ማውራት ምቾት አይሰማቸውም። በኢትዮጵያ የባህል እምነቶችና ልምምዶች ይህን ኪያጠናክሩ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ልጆች ስለ ጥቃት፣ ስለ ወሲብ እና ስለ ሥነ ተዋልዶ ጤና መረጃን በአዎንታዊ መልኩ ለማስተናገድ እምነት ሊጣልባቸው እንደማይችሉ እንሰጋለን፤ እናም ወደ ጉልምስና ሲያድጉ የሚፈልጉትን መረጃ ከመስጠት እንቆጠባለን። በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች እያደጉ ሲሄዱ ለልጆች ከዕድሜያቸው ጋር የሚስማማ መረጃን አለመስጠት በእነርሱ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር መረጃዎች[5] ያሳያሉ።

ለምሳሌ :

- ልጆች ስለ አካሎቻቸው እና ድንበሮቻቸው ወይም ስለ ሕፃናት ጥቃት እና ስለተለያዩ የጥቃት ዓይነቶች ሳያውቁ ሊያድጉ ይችላሉ። ይህ ለጥቃትና ወሲባዊ ብዝበዛ ተጋላጭነታቸውን ሊጨምር ይችላል።

- ልጆች እያደጉ ሲሄዱ ስለ ሕፃናት ከጥቃት ጥበቃ ብንነግራቸውም ባንነግራቸውም የመረጃ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ ይሄዳል። ከተለያዩ ምንጮች ስለ ጥቃት መማር ይጀምራሉ። ባለመቆጣጠራችንና እና ለዕድሜያቸው የሚመጥን እና ትክክለኛ መረጃ ባለመስጠታችን ልጆች ከሌላ ቦታ የተሳሳተ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ የበለጠ ተጋላጭ ሊያደርጋቸው እና ጥቃት ከተከሰተ በበቂ ሁኔታ ምላሽ ያለመስጠት አቅማቸውን ከፍ ሊያደርግ ይችላል።

- በኢትዮጵያ በልጆች ጥቃት ዙሪያ የዝምታ እና የማፈር ባህል አለ - በተለይ በወሲባዊ ጥቃት ዙሪያ። አንዳንድ ድርጅቶች የልጆች ጥቃት ጥበቃ ጉዳዮችን ለመቀበል ፈቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ፤ ወይም በቂ የሪፖርት እና የምላሽ ዘዴዎችን ላያዘጋጁ ይችላሉ። እነዚህ ምክንያቶች ሪፖርት የተደረገባቸው የጥቃት ጉዳዮች ዝቅተኛ ቁጥር እንዲኖራቸው አስተዋፅዎ ያደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ። ከልጆች ጋር ስለልጆች ከጥቃት ጥበቃ ያለማነጋገር የዝምታ ባህል እና በልጆች ላይ የሚደርስ የጥቃት አደጋ እንዲቀጥል ያበረታታል[6]።

5የዓለም ጤና ድርጅት ስለ በልጆች ላይ የሚደርስ የአያያዝ ችግር እውነታዎች : https://www.who.int/news-room/-fact-sheets/detail/child-maltreatment

[6]ከላይ ካለው ጋር ተመሣሣይ ነው።

ETHIOPIA HUB

ጥንቃቄ !

በብዙ የአፍሪካ ክፍሎች ልጆች የጉርምስና ዕድሜ ላይ መድረስ ሲጀምሩ ሴቶችች እና ወንዶች ልጆች ብዙውን ጊዜ ይለያያሉ። ይህ በተለይ ሴት ልጆችን ከመጠበቅ እና ከጥቃት ከመራቅ የሚጠቀሙበት ስልት ቢሆንም፣ ይህ አሠራር መገለልን ሊያበረታታ ይችላል። እንዲሁም፣ የሁሉንም የጥቃት ዓይነቶች ዋና መንስዔ የሆነውን - በሰዎች መካከል የኃይል አለመመጣጠንን እና ይህንንም አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ለማድረስ እንዴት እንደሚጠቀምበት አይመለከትም።

ስለሆነም ፕሮገራሞቻችሁ ይህንን ሁኔታ ማጠናከሪያ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። በፕሮግራሞችዎ ውስጥ ወንድና እና ሴት ልጆች እንዴት እንደሚገናኙ እና አብረው እንደሚሠሩ ያስታውሱ። ልጆች (በተለይም ወንዶች) ወደ ጉርምስና ዕድሜ ሲደርሱ ሊታመኑ አይችሉም የሚለውን አሉታዊ እምነት ድርጅትዎ እያጠናከረ አለመሆኑን ያረጋግጡ። ነገር ግን ስለ ጥቃትና ከጥቃት ጥበቃ ጉዳዮች ላይ ከመወያየት ብዙውን ጊዜ ከሴት እና ከወንድ ልጆች የተለየ ቡድኖችን እንደሚያስፈልግ ልብ ይበሉ፤ ስለሆነም ጉዳዮቹን ከመወያየት ነፃነት ይሰማቸዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የኢትዮጵያ መረጃ እና ድጋፍ ማዕከል ደህንነቱ የተጠበቀ ፐሮግራምን ከመቅረጽ የሚረዱ ጠቃሚ ምክሮችን ለማግኘት እዚህ ጠቅ ያድርጉ።

ስለ ሕፃናት ከጥቃት ጥበቃ ከልጆች ጋር ለመነጋገር ዋና መርሆዎች

- **ሥልጠና፡** ውይይቶችን የሚመራው ሠራተኛ የጥቃት ጥበቃ ሥልጠና ማግኘቱን ያረጋግጡ። በመሠረቱ፣ ይህ ልጆችን ስለማሳተፍ ወይም የልጆች ከጥቃት ጥበቃ መረጃን ማካተት አለበት።

- **ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ፡** ምንም ትኩረት የሚከፋፍሉ ነገሮች በሌሉበት እና ልጆች ምቾት በሚሰማቸው ቦታ ላይ ክፍለ-ጊዜዎችን ይያዙ። አንድ አዋቂ እና አንድ ልጅ ብቻ ጋር የሚገናኙበትን ሁኔታዎችን ያስወግዱ።

- **ምስጢራዊነት፡** ምስጢራዊነት ምን ማለት እንደሆነ በማብራራት፣ የምስጢራዊነት መሠረታዊ ሕጎችን በማዘጋጀት እና የሌላውን አስተያየት እና አመለካከት በማክበር ይጀምሩ።

- **ተሳትፎ፡** በተለያየ ዳራ ለመጡ ልጆች (እንደ ኃይማኖት፣ ዘር፣ አካል ጉዳተኛነት ያሉ) በርዕሶች ላይ ለመወያየት እና ሀሳቦችን በፈጠራ መንገዶች ለማጋራት ቦታን ይስጡ - ለመሳተፍ ከፈለጉ። ይህ ልጅዎ በቅንብርዎ ውስጥ አደጋዎችን የሚጠብቅበትን በበለጠ ለመረዳት ይረዳዎታል። ይህ በእርስዎ ዙሪያ ያሉ ልጆችን ከጥቃት የመጠበቅ አደጋዎች በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ ያግዝዎታል።



- **የተለያዩ ቡድኖች፡** ተመሣሣይ ዕድሜ እና ፆታ ካላቸው ልጆች ጋር ወሲባዊ ጥቃትን እና ሌሎች የጥቃት ዓይነቶችን ይወያዩ። ወንድና ሴት ልጆችን አንድ ላይ አይቀላቅሉ እና / ወይም ታናናሾችን እና ትልልቅ ልጆችን አንድ ዓይነት ፆታ ቢኖራቸውም አንድ ላይ አያጣምሩ።

- **ከዕድሜ ጋር የሚስማማ፡** መማማሩን ለማጠናከር ተገቢ እና ከዕድሜ ጋር የሚስማሙ ስዕሎችን፣ ታሪኮችን እና አካባቢያዊ ምሳሌዎችን ይጠቀሙ።

- **ለስሜቶች ይጠንቀቁ፡** ማንኛውንም የስሜት ለውጦች ያስታውሉ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እረፍት ይውሰዱ እና ከዚያ ይቀጥሉ (ከተቻለ)።

- **በመደበኛነት መነጋገር፡** ከልጆች ጋር ስለ ልጅ ከጥቃት ጥበቃ በመደበኛነት ለመወያየት ያቅዱ። እነዚህን ክፍለ -ጊዜዎች መርሐ ግብር ማስያዝ ይችላሉ።ለምሳሌ፡ ከእያንዳንዱ ሥርጭት በፊት፣ በወር አንድ ጊዜ፣ አንድ ልጅ ወይም ወላጅ አንድ ፕሮግራምን ሲቀላቀሉ፣ እና ከዚያ በኋላ በየዓመቱ ከሁለት እስከ ሶስት ጊዜ።

- **ማናቸውንም ቅሬታ በአግባቡ መቀበል፡** በልጆች ከጥቃት ጥበቃ ዙሪያ የሚደረጉ ውይይቶች የጥቃትን ትዝታዎች ሊያስታውሱ እና ልጆች የጥቃት ክስተቶችን ሪፖርት እንዲያደርጉ ሊያደርጋቸው ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ለልጁ/ለልጅቷ ፈጣን ማጽናኛ ይስጡ፣ ያዳምጡ እና በድርጅትዎ የሪፖርት ዘዴ በኩል ሪፖርት ያድርጉ።

ስለ ልጆች ከጥቃት ጥበቃ ከልጆች ጋር እንዴት መነጋገር እንደሚቻል

ከልጆች የጥቃት ጥበቃን በሚገልጹበት ጊዜ የተለያዩ የልጆች ቡድኖች ሊረዷቸው የሚችሉትን ቋንቋ እና ቃላትን መጠቀም ያስፈልግዎታል። ይህ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ልጆች የሚከተሉትን እንዲረዱ ይፈልጋሉ።

- የሕፃናት ጥቃት ምን እንደሆነ እና ሁሉንም የሕፃናት ጥቃት ዓይነቶችን
- ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የድርጅቱን ቁርጠኝነት
- ራሳቸው፣ ጓደኛቸው ወይም የሚያውቁት ሰው እየተጎዳ ከሆነ ስጋት እንዴት እንደሚያሳውቁ ወይም ሪፖርት እንደሚያደርጉ

ያስታውሱ !

የልጆች ከጥቃት ጥበቃ ከወሲባዊ የጥቃቶች ዓይነቶች ባሻገር ይመለከታል። የልጆች ከጥቃት ጥበቃ አካላዊ ጥቃትን፣ ወሲባዊ ጥቃትን፣ ወሲባዊ ብዝበዛን፣ ወሲባዊ ትንኮሳን፣ ችላ መባልን/መዘንጋትን፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቃትን እና ሌሎች በልጆች ላይ የሚደርስ ጉዳትን እና ጥቃቶችን ጨምሮ ሁሉንም የጉዳት ዓይነቶች ይመለከታል። ሁሉም ሠራተኞች ከልጆች የጥቃት ቅሬታን እንዴት እንደሚቀበሉ እና በቀጣይነት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው።

ያስታውሱ !

በልጆች ላይ የሚፈጸመውን ጥቃት፣ በተለይም ወሲባዊ ጥቃትን ለልጆች ማስረዳት ከባድ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ፣ እንደ ዕድሜያቸው እና የዕድገታቸው ደረጃ ልጆች ለመረዳት ይከብዳቸው ይሆናል። ውይይቶችዎን ሲያካሂዱ ሁል ጊዜ ከላይ የተዘረዘሩትን መርሆዎች ያስታውሱ።

በቀላሉ የሚቀርብ፣ ተግባቢ እና ዘና ያለ ይሁኑ፡ ልጆች የሚያነጋግራቸው ሰው የተረጋጋ፣ በራስ መተማመን ያለው እና ተግባቢ በሚሆንበት ጊዜ ዘና ይላሉ። ከልጆች ጋር ስለ ልጆች የጥቃት ጥበቃ በሚወያዩበት ጊዜ በራስ መተማመንን፣ ጓደኝነትን እና ቀላል ብሎ መቅረብን ያሳይዋቸው።

ETHIOPIA HUB

የአንድ ድርጅት ጥቃትን ለመከላከል እና ምላሽ መስጠት የድርጅቱን ቁርጠኝነት እንዴት መግለፅ እንደሚቻል

ዓላማ፡ ልጆች ማን እንደሆናችሁ እና ለምን እንደምታናግሯቸው ማወቅ ይፈልጋሉ። ማን እንደሆንክ/ሽ እና የድርጅትህን/ሽን ቁርጠኝነት በማብራራት መጀመር ይቻላል።

“እኛ XX ድርጅት እንባላለን። ከ [እንደ አስፈላጊነቱ ይጠቀሙ፡ ወንዶች / ሴቶች / ማኅበረሰቦች / ልጆች / አካል ጉዳተኞች ወዘተ] ጋር [እንደ አስፈላጊነቱ ይጠቀሙ፡ ውሃ / ምግብ / ትምህርት ቤት / የሥራ ዕድል ወዘተ] በተገቢው መንገድ እንዲሟሉ እንሠራለን። ለሚቀጥሉት XX ወራት/ ዓመታት በዚህ ቦታ እንሠራለን። እኛ XX ከሚባል ሌላ ድርጅት ጋር አብረን እንሠራለን።”

“ በድርጅታችን ያለን ሁላችንም እዚህ ያለነው እናንተን ለመርዳት ነው። ሁሉም ሰዎቻችን ደግ መሆናቸውን፣ በፍትሃዊነት የሚያገለግሉ እና እናንተን ወይም በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለን ማንም ሰው እንደማይጎዱ ለማረጋገጥ እንፈልጋለን። እኛ ይህንን ከጥቃት ጥበቃ ብለን እንጠራዋለን ይህም የእናንተን ደህንነት መጠበቅ እንደምንፈልግም ለማሳየት ነው። እናንተን ከጥቃት ለመጠበቅ የምናደርጋቸው ጥቂት ነገሮች አሉ። ይህንን ከእናንተ ጋር መወያየት ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ነው። የእናንተን ደህንነት ለመጠበቅ እንደምንፈልግ ከወላጆቻሁ ጋር እንነጋገራለን። እናንተን እንዴት ከጥቃት እንደሚጠብቁ እና ስለ እናንተ ሁኔታ ስጋት ካለባቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሠራተኞቻችንን አሠልጥነናል።”

ከልጆች የጥቃትን ፍቺዎች እንዴት መግለፅ እንደሚቻል

ዓላማ፡ ይህ ክፍል ከተለያዩ የዕድሜ ቡድኖች ጋር ውይይቱን መጀመር በምትችልባቸው በተለያዩ መንገዶች ላይ የተለያዩ ምክሮችን ይሰጥዎታል።

በልጆች ላይ የሚደርስ ጥቃትን ከመግለጽ ሊወስዷቸው የሚችሏቸው በርካታ መንገዶች አሉ። ከልጆች ጋር ውይይት ከመጀመር ጠቃሚ መንገድ ከዕድሜ ቡድኑ ተስማሚ የሆነ ታሪክ ወይም አሳታፊ ልምምድ መጠቀም ነው። አንዳንድ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ[7]።

- የሰውን አካል መሳል ("የሰውነት ካርታ") እና ያንን ተጠቅመው በልጆችን ስሜት እና የግል ስጋቶች እና ጉዳዮች መነጋገር
- የተለያዩ ሁኔታዎችን እና የሰዎች ዓይነቶችን ለማሳየት አሻንጉሊት ወይም ድራማን መጠቀም
- ማኅበረሰብን ወይም ቦታን መሳል፣ ለምሳሌ የትምህርት ቤት/የፕሮግራም ቦታ፣ እና ያንን ተጠቅሞ ልጆች በበለጠ/ በጥቂቱ የት ደህንነት እንደሚሰማቸው ማዋራት እና ለምን እንደሆነ ለመነጋገር

በዚህ መመሪያ መጨረሻ ላይ በተሳትፎ ላይ ተጨማሪ መገልገያዎች አሉ።

ለትናንሽ ልጆች የሚከተሉትን በመናገር መጀመር ይችላሉ፡-

ጥቃት በተለያየ መልኩ ይመጣል። ጥቃት አንድ ሰው/አንዲት ሴት እናንተን ለመጉዳት አንድ ነገር ሲያደርግ/ስታደርግ ወይም ማድረግ ያለበትን/ያለባትን ሳያደርግ/ሳታደርግ እና ይህም እናንተን ወደ መጎዳት የሚመራ የሚመራ ከሆነ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ቢመታችሁ፣ ወይም በጥፊ ቢመታችሁ፣ እንደ ሞኝ ወይም የማይጠቅም በመቀጠር በመጥፎ ስም ቢጠራችሁ፣ በማንነታችሁ ምክንያት መጥፎ ቢያደርግባችሁ እነዚህ ሁሉ የጥቃት ዓይነቶች ናቸው፤ እናም ስህተት ነው።" ወይም

[7] ከ የሕፃናት አድን ድርጅት ሕፃናትና ወጣቶች የሚመች አሳታፊ የድርጊት ምርምር መሣርያ የተወሰደ https://resourcecentre.savethechildren.net/library/child-and-youth-friendly-participatory-action-research-toolkit

የጥቃት ምድቦችን[8] መዘርዘር እና ልጆቹ ለእያንዳንዱ ምድብ ባህሪያትን መለየት ይችሉ እንደሆነ መጠየቅ ይችላሉ።

ወይም

በኢትዮጵያ አንዳንድ የአማርኛ የልጆች መዝሙሮች/ዘፈኖች እንደ “በዛ በበጋ” እና “እቴሜቴ” የሕፃናትን ጠለፋ እና ተገቢ ያልሆኑ (ከዕድሜ በታች) ግንኙነቶችን ሀሳብ ያጭራሉ።

እነዚህ የሕፃናት መዝሙሮች/ዘፈኖች ተገቢ ያልሆነ መልዕክት እንደሚያስተላልፉ ልጆቹን ማስረዳት ድንበሮችን እንዲያስተውሉ ይረዳቸዋል።

ቢደረጉ ጠቃሚ የሆኑ ተጨማሪ ነጥቦች፡

“ማንም ሰው (ከእናታችሁ / ከአባታችሁ / ከተንከባካቢያችሁ በስተቀር) የእናንተን የግል የሰውነት ክፍሎች/ብልት መንካት ወይም ማየት መፈለግ የለበትም። የእነሱን እንድታዩ ወይም እንድትነኩ መጠየቃቸውም ስህተት ነው። ማንም ሰው ስለእነዚህ የሰውነት ክፍሎች ምንም ቢናገር ይህ ስህተት ነው።”

“አንድ ሰው የማይመቻችሁን ነገር እንድታደርጉ ቢጠይቃችሁ ወይም በውስጣችሁ የሆነ ችግር እንዳለ ከተሰማችሁ ይህ ነገር ምናልባት ስህተት ነው ማለት ነው። እንዲሁም ፍርሃት እና ድንጋጤ ሊሰማችሁ ይችላል። የሆነ ነገር ስህተት እንዳለ የሚነግራቸሁ ይህ አእምሯችሁ ነው።”

---

[8] ወሲባዊ ጥቃት፤ ወሲባዊ ብዝበዛ፤ አካላዊ፤ ሥነ ልቦናዊ፤ ችላ ማለት/መዘንጋት

ለትላልቅ ልጆች (ጎረምሶች/ኮረዶች) ስለ ወሲባዊ ጥቃት ሲናገሩ፣ እንደዚህ ማለት ይችላሉ።

"ስለ ሰውነታችሁ እና ስለግል ብልቶቻችሁ አንዳንድ ጥያቄዎች ሊኖሯችሁ ይችላል። ይህ የተለመደ ነው። ስለጥያቄዎቻችሁ ለማውራት ከሚቀላችሁ ዶክተር፣ አስተማሪ፣ የማኅበረሰብ አባል፣ ወላጆች ወይም የታመነ አዋቂ ሰውን ጋር መወያየት ትችላላችሁ።"

"ከእናንተ ጋር ልዩ ጓደኛ መሆን የሚፈልግን ሰው ወይም የምትፈልግን ሴት ታውቁ ይሆናል[9]። ይህ ሰው ወይም ይቺ ሴት ለእናንተ በጣም 'ጥሩ' እንደሆነ/ነች የሚሰማችሁ እና ለእናንተ ምቾት ባይሰጣችሁም እርሱ/እርሷ ምቾት እንዲሰማው/ማት የሚያደርግ ነገር እንድታደርጉ ሲጠይቅህ/ሽ ሰውዬውን/ሴትዮዋን ላለማስቆጣት ልትፈልጉ ትችላለህ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ምርጫ እንዳላችሁ በማስታወስ እምቢ ማለት ትችላላችሁ። ይህ ሰው/ይህቺ ሴት እውነተኛ ጓደኛ ከሆነ/ች ፣ ምርጫ እሁን ያከብራል/ታከብራለች እና ጓደኛችሁ መሆንም አያቆምም/አታቆምም። ይህ ሰው የማትፈልጉትን ነገሮች መጠየቁን/መጠየቋን ከቀጠለ/ች ወይም እንድትፈሩት/ሯት ማድረግ ከጀመረ/ች ለወላጅ ወይም ለምታምኑት ሰው ተናገሩ።"

ስሜታዊ ጥቃት ስውር ሊሆን ይችላል፣ አንዳንድ ጊዜ ልጆች ላያውቁት ይችላሉ። ስሜታዊ ጥቃትን ለማብራራት፣ እንዲህ ይበሉ፡-

"አንድ ሰው በመጥፎ ስሞች ተጠቅሞ ቢጠራችሁ ለምሳሌ ደደብ ወይም የማትረባ/ቢ ነህ/ነሽ ወይም ማንኛውም ነገር በትክክል ማድረግ የማትችሉ ዓይነት ስሜት እንዲሰማችሁ ካደረገ/ች ይህ ስህተት ነው። ይህ ክስተት ካጋጠመ የስሜታዊ ጥቃት ዓይነት መሆኑን አስታውሱ። ያን ሰው/ያቺን ሴት አትመኑት/ኗት። ሰውዬው/ሴትዮዋ የተሳሳተ/ች እና የሚለው/የምትለው ሁሉ የእናንተ እንዳልሆኑ በመንገር ተገቢ ያልሆኑትን ስሞች ተጠቅሞ መጥራቱን/ቷን እንዲያቆም/እንድታቆም ጠይቁ።"

9የጉርምስና ዕድሜ እና ደረጃ. በዓለም ዙሪያ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ሴት ልጆች ልምዶችን መረዳት. *2017*

ልጆች የጥቃት አደጋ እንደተጋረጠባቸው ከተሰማቸው ማን ማድረግ እንዳለባቸው እንዴት ማውራት እንደሚቻል

ልጆች የሚያሳስባቸው ጉዳይን ለድርጅቱ እንዴት እንደሚያስረዱ መረዳት አለባቸው፣ ይህን ለማድረግ በራስ መተማመን ሊሰማቸው ይገባል። በሐሳብ ደረጃ ልጆችን ከእርስዎ ጋር እንዴት እንደሚያሳስቧቸው ይጠይቃሉ (በማኅበረሰብ ላይ የተመሠረተ የቅሬታ ዘዴን እንዴት ማዋቀር እንደሚቻል ለ የሀብት እና ድጋፍ ማዕከል ምንጭ እዚህ ጠቅ ያድርጉ)። እነዚያ ዘዴዎች ከተዘጋጁ፣ ሕፃናት እንዲረዷቸው እና በራስ መተማመናቸውን እንዲያሳድጉ መርዳት አለብዎት።

የእናንተ ጥፋት አይደለም፡

"ምንም ተነግሯችሁ ቢሆን፣ የተነገራችሁ/የተናገረቻችሁ ማንምቢሆን ወይም ያደረጋችሁት ቢመስላችሁ፣ ጥቃት በጭራሽ የእናንተ ጥፋት አይደለም፣ ጥቃትም አይገባችሁም ። ሰው ሲጎዳን መበሳጨት፣ መቆጣት፣ መፍራት እና ግራ መጋባት የተለመደ ነው። ራስን መጠራጠርም የተለመደ ነው። ነገር ግን ራሳችሁን አትውቀሱ ወይም ሌሎች ምን እንደሚያስቡ ወይም በእናንተ ላይ ይናደዳሉ ብላችሁ ብላችሁ አትጨነቁ። ምንም እንኳን ስህተት እንደሠራችሁ ቢሰማችሁንም የወይም ነገሮችን በተለየ መንገድ ማድረግ እንደነበረባችሁ ብታስቡምይህ ማንም ሰው እንዲጎዳችሁ ምክንያት መሆን አይችልም ።"

የፍርሃት/ስጋት ስሜት፡

"ሰዎች ሲጎዱን "አንተ/አንቺ እኮ ጓደኛዬ ነህ/ነሽ፣ እኔ እወድሃለሁ/ሻለሁ፣ ይህ የእኛ የብቻችን ምስጢር ነው" እና የመሣሠሉትን ነገሮች ሊሉን ይችላሉ። በሌላ ጊዜ ደግሞ "ጓደኛዬ ከሆንክ/ሽ ይህንን ምስጢር ትጠብቃለህ/ትጠብቂያለሽ"፣ ሊሉን ይችላሉ። በሌላ ጊዜ ደግሞ "ይህንን ነገር ለሰው ከተናገርክ/ሽ ቤተሰቦችህ/ሽ አይወዱህም/ሽም" ብለው ሊያስፈራሩን ይችላሉ። እንደ ኃይማኖት/ባህል ያሉ ነገሮችን በመንጠቀም "አንተን/አንቺን ማስተማር/ማሰልጠን የእኔ ግደታ ነው" በማለት ሰበቦችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። አናንተን በቀጣይነት ለማታለልና ለመጉዳት የሚጠቀሙበት ውሸቶች እና የማታለያ ዘዴዎች ስለሆኑ አትመኗቸው። "

“አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የጠየቁንን ማንኛውንም ነገር ካደረግን፣ ወይም ያደረጉትን ማንኛውንም ነገር ወይም ማድረግ የነበረባቸውን ነገር ግን ሳያደርጉት የቀሩትን ነገሮች ሪፖርት ካላደረግን ለቤተሰቦቻችን ገንዘብ ወይም ምግብ እንደሚሰጧቸው ሊነግሩን ይችላሉ። እነሱ የጠየቁትን ካላደረግክ ወላጆቻችን ችግር ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ እና ከእነሱ ጋር ያደረግከውን ነገር በፍቃደኝነት እና በስምምነት እንዳደረግን ለሰዎች እንደሚነግሩብን እና ማንም እንደማያግዘን እና እንደማያምነን ሊነግሩን ይችላሉ። ይህን ሲሉን ልንፈራ እንደምትችል ይታወቃል ግን አንማናቸው። ይህንን የሚሉን የሚፈልጉትን መጥፎ ነገር ሊያደርጉብን፣ የሚያደርጉትን እና ማድረግ የነበረባቸውን ነገር ግን ያላደረጉትን ለሰዎች እንዳንናገርባቸው ለማድረግ ነው። ስለሁሉም ነገር የተናገሩንን ጨምሮ ለቤተሰብ ወይም ለታመነ አዋቂ ሰው እንናገር።”

አስቸኳይ እርምጃዎች ፡

“የሚጎዳንን ሰው እንዲያቆሙ እና መሄድ እንደምንፈልግ መንገር ምንም ችግር የለውም። ሰዎች በሌሎች መነካት የሌለበትን የሰውነት አካላችንን ለመንካት ወይም ለማየት ከፈለጉ ወይም የራሳቸውን እንድንነካ ከጠየቁን ወይም የማይመቸንን ነገር ሲያደርጉ፣ ወደ መጸዳጃ ቤት መሄድ እንደምንፈልግ ወይም መውጣት እንደምንፈልግ መናገር እንችላለን። የጠየቁንን ማድረግ የማንፈልግ ከሆነ ለእርዳታ መጮህ እንችላለን፣ ለድርጅታቸው ወይም ለታመነ አዋቂ ሰው እንደምናሳውቅ እንናገር። ከቻልን ወይም ከፈለግን ለመሮጥ

“አንዳንድ ጊዜ ጥቃት አድራሾች ሊነኳችሁ ሲፈልጉ ስለ ሰውነታችን ማውራት ሊጀምሩ ይችላሉ። እንዴት ቆንጆ እንደሆንን፣ እንዴት እንደሚወዱን ወይም ልዩ ጓደኛችን መሆን እንደሚፈልጉ ሊነግሩን ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ በአጠገባችን ሲሄዱ ጡታችንን ሊቦርሹ ወይም ሊነኩ ይችላሉ እና ይህ አጋጣሚና ስህተት ነው ሊሉ ይችላሉ። ይህ አጋጣሚ ከተከሰተ ስህተት መሆኑን አስታውሱ፣ ሊነኳችሁ እንደሚፈልጉም አስተውሉ። ያደረጉትን ነገር እንዳልወደዳችሁትና እና ሪፖርት እንደምታደርጉ ንገሯቸው። ከእነርሱ በመራቅ ለታመነ አዋቂ ጉዳዩን ተናገሩ። በተቻለ መጠን ከእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር በጭራሽ ብቻችሁን አለመሆናችሁን አረጋግጡ፤ በተጨማሪም የሆነ ቦታ እንድትገናኙ ከጠየቋችሁ አትሂዱ (አብሮህ ሊሄድ ከሚፈልግ ጓደኛችሁ ጋር ቢሆንም እንኳን አትሂዱ) ነገር ግን ስለሁኔታው ለታመነ አዋቂ ተናገሩ።”

ስጋቶችን ማሳወቅ :

“ሁልጊዜ ለምናምነው ሰው አናሳውቅ። ይህ የምናምነው ሰው እናታችን፣ አባታችን፣ አስተማሪያችን ወይም በድርጅታችን ውስጥ ያለ ሠራተኛ ሊሆን ይችላል”። የታመነ አዋቂ ሰው የግድ የቤተሰብ አባል ማለት እንዳልሆነ ለልጆች ይንገሩዋቸው[10]። “የታመነ አዋቂ ሰው ማንኛውን ነገር ለመንገር ምቾት የሚሰጡን እና ደህንነት እንዲሰማን ማድረግ የሚችሉ ሰዎች ናቸው። የታመነ አዋቂ ሰው እርዳታ በምንፈልግበት ጊዜ ያለ ስጋት ልናናግራቸው የምንችላቸውን ሰዎች ሲሆኑ፣ ከዚህ በፊት የረዱን እና/ወይም ደህንነት እንዲሰማን የሚያደርግጉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።”

[10] ደህንነታቸው የተጠበቀ ልጆች። የታመነ አዋቂን መለየት *https://www.safesecurekids.org/sites/default/files/SSK-Identifying%20Trusted%20Adults_VD.pdf*

ጉዳት ስለሚያደርሱባችሁ ሰዎች ሪፖርት ብታደርጉ በጭራሽ ችግር ውስጥ አትገቡም። የሚጎዳችሁን ሰው ብታሳውቁ ችግር ውስጥ እንደምትገቡ ከተሰማችሁ፣ የሚታመን አዋቂ አግኙ፣ ግለሰቡን/ቧን በግል ለማነጋገር እንደምትፈልጉ በመጠየቅ የተከሰተውን ሁኔታ ምቾት በሚሰማችሁ መንገድ ግለጹ። ለአዋቂ ሰው ጉዳዩን ስትነግሩ አዋቂው ሰው ለድርጅቱ የመናገር ግዴታ አለበት/ባት።"

ስልክ ማግኘት ለሚችሉ ልጆች፤ በተለይም ዕድሜያቸው ከ 15-17 ለሆኑ ሕፃናት፣ ለሚያምኗቸው አዋቂ ሰዎች ጋር የሚግባቡበትን የኮድ ቃል ሊሰጧቸው እና ምቾት ሳይሰማቸው ወይም ደህንነቱ ባልተጠበቀ ሁኔታ ውስጥ ሆነው እንዲደርሱላቸውና እንዲወስዷቸው ሲፈልጉ ብቻ ጥቅም ላይ እንደሚውል ከአዋቂው ጋር መስማማት ይችላሉ።

"የሚመቻችሁ ከሆነ በስውር የጽሑፍ መልዕክት መላክ ወይም ወደ ታመነ አዋቂ መደወል እና ስልካችሁን በድምጽ ማጉያ ላይ ማድረግ ትችላላችሁ። ይህንን በምናደርግበት ወቅት የምስጢር ቃሉን መናገር፤ የምስጢር ቃል ከሌለ 'አቁም' እና 'አይሆንም' የሚሉትን ቃላቶች መደጋገም። በተጨማሪም የት እንዳላችሁ መናገር፤ ይህም አዋቂው ሰው ችግር ውስጥ እንደሆናችሁ አውቆ ወዳላችሁበት መጥቶ ድጋፍ እንዲሰጣችሁ ይረዳዋል።"

ስለ ሌላ ልጅ የስጋት ሪፖርት ማድረግ:

"ሌላ ልጅ በድርጅቱ ሰው ተጎድቷል/ታለች ወይም ተበድሏል/ላለች ብላችሁ ከጠረጠራችሁ ይህንን ለታመነ አዋቂ አሳውቁ። አንዳንድ ጊዜ ህፃኑ/ኗ ሊፈራ/ልትፈራ ወይም ምንም መናገር አይችል/አትችል ይሆናል፤ እና ሪፖርት ካደረግነለት/ላት እየረዳነው/ናት ነው። እንዲሁም ራሳቸው ሪፖርት እንዲያደርጉ ማበረታታት ትችላላችሁ። ለጓደኞቻችሁ አትንገሯቸው፤ ምክንያቱም ምስጢሩን መጠበቅ ስለማይችሉ ወይም ተበዳይ ላይ ሊቀልዱ ስለሚችሉ፤ ይህ ደግሞ ተጎጂውን/ዋን የበለጠ ሊያሳዝንና እና ሊጎዳ ይቻላል። ጉዳዩን ከእናንተ ጋር አቆዩት እና አዋቂው ትክክለኛውን ነገር እንደሚያደርግ እመኑ።"

ቀጥሎ ምን ይሆናል?

“እንዴ ከአዋቂ ሰው ወይም ከድርጅቱ ሪፖርት ካደረጋችሁ ድርጅቱ ሪፖርቱን በምስጢር ይይዙታል። ሁኔታውን ከመረዳት እና አስፈላጊውን ውሳኔ ለማድረግ ይሞክራሉ። ይህም አንተን/አንቺን ማነጋገርን ሊያካትት ይችላል።”

ውይይቱን መዝጋት

“አንድ ሰው ሲጎዳችሁ ወይም ጥቃት ሲያደርስባችሁ መናገርን ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፤ ምን ሊሆን ይችላል ብላችሁ ትፈሩ ወይም ትሰጉ ይሆናል። አስታውሱ ብቻችሁን አይደላችሁም እንዲሁም ለእናንተ የሚያስቡ ሰዎች አሉላችሁ። ሁልጊዜ ይህ በጭራሽ የእናንተ ስህተት እንዳልሆነ አስታውሱ እንዲሁም ሪፖርት በምታደርጉበት ጊዜ አንድ ሰው እናንተን ለመርዳት ይሞክራል።”

አስታውሱ !

መጨረሻው እንደ መጀመሪያው አስፈላጊ ነው። ለመውጣት እና እርምጃ ለመውሰድ መቸኮል የለብዎትም። ይረጋጉ ! ልጆቹን ለተሳትፏቸው አመስግኑ እና ጥያቄ ካላቸው ወይም የሚናገሩት ነገር ካለ ያረጋግጡ/ጠይቋቸው። የእርስዎን ወይም የጥቃት ጥበቃ ተጠሪውን/ዋን ወይም የድርጅቱን የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴ አድራሻ ዝርዝሮችን እንድትሰጧቸው ይመከራል።

የጥቃት ምልክቶችን እንዴት መለየት እና ይፋ ማድረግ እንደሚቻል

ዓላማ: ይህ ለእርስዎ ነው፣ እንደ ባለሙያ! ይህ ክፍል የሆነ ችግር ሲፈጠር፣ ምን መናገር እንዳለብዎ እና ምን መናገር እንደሌለብዎ ለማወቅ የሚረዱ ጠቃሚ ምክሮችን ይሰጥዎታል።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሠራተኞች የሕፃናትን ከጥቃት ጥበቃ አደጋዎችን ማወቃቸው እና ጥቃት ሲፈጸም ማወቃቸው አስፈላጊ ነው። ብዙ ጊዜ ልጆች ጥቃት እና ከጥቃት ጥበቃ ላይ ውይይቶች ሲደረጉ ጥቃትን ያሳውቃሉ። ሠራተኞችም የሕፃናቱ ባህሪያት ወይም ሌሎች ሕጻናቱ ጥቃት እየደረሰባቸው መሆኑን የሚጠቁሙ ምልክቶችን ሲያሳዩ ሊያሳስባቸው ይችላል። [11]

ጠቃሚ ምክር:

የሕፃናት ከጥቃት ጥበቃ ግንኙነቶች አንድ ጊዜ የሚታይ ወይም መደበኛ ያልሆነ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ቢሆንም የልጆችን ባህሪ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። የልጆችን ባህሪ ይገንዘቡ እና ሁልጊዜም ስሜትዎን ያክብሩ/ውስጥዎን ያዳምጡ።

[11] ከልጆች ጥቃት እርዳታ የተወሰደ። በልጆች ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ በደል ልናውቃቸው የሚገቡ ምልክቶች.
www.nneca.org.uk

የጥቃት ምልክቶች

- ከዚህ ቀደም ያላሳዩትን የሰው ወይም ቦታን መፍራት ባህሪ ማሳየት። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግለሰቡ በሠራተኞችዎ መካከል ‘የታመነ’ ቢሆንም እንኳን[12] እርምጃ ይውሰዱ።
- ምንጩ ሊገለጽ የማይችል ገንዘብ እና/ወይም ስጦታዎች ወይም ስለ አዲስ/ሚስጥራዊ ጓደኛ ማውራት
- በወሲባዊ ነገሮች ላይ አዲስ ፍላጎት ማሳየት፣ ሥዕሎች፣ ከባህሪ ውጪ የሆኑ የወሲብ ቃላት አጠቃቀም
- የባህሪ እና/ወይም የስብዕና ድንገተኛ ለውጥ፣ ለምሳሌ ግጭቶችን መምረጥ፣ መጨናነቅ፣ የሃሣብ መከፈል/ትኩረት ማጣት፣ መነጠል ወይም መራቅ
- በአለባበስ እና በውጫዊ ገጽታ ላይ ምክንያቱ ሊገለጽ የማይችል ለውጥ ማሳየት፤ ለምሳሌ ይበልጥ ስሜት ቀስቃሽ ወይም የተዝረከረከና ንፅህና የጎደለው አለባበስ
- ወደ መታጠቢያ ቤት ሲሄዱ ሕመም መሰማት
- በሰውነት ላይ ምክንያቱ ያልታወቀ ጉዳት፣ የዓይን እብጠት፣ በጀርባ፣ በእግር፣ በእጅ፣ወዘተ ላይ ያሉ ምልክቶች
- ራስን ማግለል፣ ቁጥብ መሆን እና ከጓደኞቻቸው ጋር መጫወት አለመፈለግ
- ሁልጊዜ የሌሎችን ማፅደቅ/አዎንታ መፈለግ፣ ስለራሳቸው እርግጠኛ አለመሆን፣ ራሳቸውን መጠራጠር እና/ወይም ቀላል ውሳኔዎችን ከራሳቸው ማድረግ አለመቻል

የጥቃት ምልክቶችን ከልጆች ጋር ከተወያዩ ምልክቶቹን ያካፍሏቸው እና ሌላ የሚጨምሩት ምሳሌዎች ካላቸው ይመልከቱ። ትናንሽ ልጆች ላይ ጨምሮ በሌሎች ልጆች ላይ የጥቃት ምልክቶች ካዩ ልጆች ሪፖርት እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው።

[12]ለጥቃት ጥበቃ ሪፖርት ምላሽ መስጠትን (ምን ማለትና ማድረግ እንዳለብን) በክፍል 3 ተብራርቷል።

ጥበቃና ከጥቃት ጥበቃ ላይ ከልጆች ጋር ሲነጋገሩ የጥቃት መግለጫ ከደረሰዎት፡-

ያድርጉ	አያድርጉ
ምቹ ቦታ ይምረጡ። ሁልጊዜ ከልጅ ጋር ምንም ዓይነት ያጋጠመውን/ማትን የጥቃት ክስተትን ሲወያዩ መስተጓጎል የማይኖርበትን ምቹ እና ምስጢራዊ የሆነን ቦታ ይምረጡ። ልጆች ከውይይት የማይመች የውይይት መቆራረጥ/መስተጓጎል ሊኖር እንደሚችል በሚያውቁት ቦታ ሊያናግርዎ ሲቀርቡ ምክንያትዎን በማስረዳት ሌላ ቦታ መቀየር የሚያስፈልጋችሁ ያስረዷቸው። ለምሳሌ፡ እንዲህ ይበሉ፡- “ይህን ስለነገርከኝ/ሽኝ አመሰግናለሁ። የምትነግረኝን/ሪኝን ነገር በቁም ነገር እወስደዋለሁ እና ሙሉ ትኩረቴን ልሰጥህ/ሽ እፈልጋለሁ። ስለዚህ ወደ (ቦታው መጥቀስ) እንድንሄድ እፈልጋለሁ። ይህ ለአንተ/ቺ ችግር አለው?”	ጥቃት መፈጸሙን መካድ። ልጆች በድርጅትዎ ውስጥ ጥቃት እንደተፈጸመ ሲነግርዎት ይህ የተለመደ ምላሽ ነው። ልጆች የሚናገሩትን በማዳመጥ ያክብሯቸው። ለምሳሌ እንዲህ ይበሉ፡ “ይህን ስለነገርከኝ/ሽኝ አመሰግናለሁ። መናገር በመቻልህ/ሽ በጣም ጎበዝ ነህ/ሽ። አምኜሃለሁ/ሻለሁ እናም ይህንን በቁም ነገር እወስደዋለሁ።”
ማረጋገጫ ይስጡ፣ ደጋፊ እና የማይፈርዱ ይሁኑ። ለምሳሌ እንዲህ ይበሉ፡- “ስለነገርከኝ/ሽን አመሰግናለሁ። የነገርከኝን/ሽኝን ሁሉ አምንሃለሁ/ሻለሁ እናም አንተን/አንቺን ለመርዳት የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ”	የሰሙት ነገር ሁሉ የሚያስደነግጥ ቢሆንም ድንጋጤን፣ ፍርሃትን ወይም አስፈሪ ሁኔታን አያሳዩ። ይህን ካደረጉ ሕፃኑ/ኗም ያንኑ ያንፀባርቃል/ታንፀባርቃለች። ሁልጊዜ በራስ መተማመንን እና ድጋፍ መስጠትን ያሳይዋቸው።

ያድርጉ	አያድርጉ
የተረጋጋ ሁኔታን፣ በራስ መተማመንን ያሳዩ፤ እንዲሁም የዓይን ግንኙነትን ይጠብቁ። እነዚህ ሁሉ ሕፃኑ/ኗ ምናልባት ደህንነቱ/ቷ ያልተጠበቀ እንደሆነ ሲሰማው/ትና ግራ በተጋባበት ጊዜ በራስ መተማመንን፣ ዋስትናን እና መተማመንን የሚያበረታቱ በቃል የማይገለጽ ምልክቶች ናቸው። ለምሳሌ እንዲህ ይበሉ፡- “ትክክለኛውን ነገር እየሠራህ/ሽ ነው። አንተን/ቺን ለመርዳት የምችለውን አደርጋለሁ። በመንገርህ/ሽ ትክክለኛውን ነገር አድርገሃል/ሻል።"	ውሳኔዎች አያድርጉ፤ ሁልጊዜ ድጋፍን ያሳዩ።
በጥንቃቄ ያዳምጡ እና ግምቶችን አይውሰዱ።	ልጁን/ልጅቷን በጥያቄ መመርመር
በዚህ ጊዜ ከመናገር ይልቅ ማዳመጥ የበለጠ አስፈላጊ ነው። ልጁ/ልጅቷ የሚመቸውን/ቻትን ፍጥነት፣ ቃላት እና ቋንቋ እንዲጠቀም/እንድትጠቀም ይፍቀዱ።	ይህ የተለመደ ምላሽ ነው፤ ብዙ ለማወቅ በመጓጓታችን አንዳንድ ጊዜ ብዙ ጥያቄዎችን መጠየቅ እንጀምራለን። ይህንን ከማድረግ ይቆጠቡ፤ ልጁን/ልጅቷን ግራ ሊያጋባ ስለሚችል እና ክስተቱን እንደገና ለመድገም ከባድ ስለሚያደርግባቸው። እንዲሁም፣ ጥያቄዎችን የሚጠየቁት በጥቃት ጥበቃ ተጠሪ ወይም በሌላ አገልግሎት ሰጪ ባለሞያ ብቻ ነው። ልጆች ከሚያስፈልገው በላይ ታሪካቸውን እንዲያካፍሉ ከመጠየቅ ይቆጠቡ። ልጁን/ልጅቷን አታቻኩሏቸው እንዲሁም ምን ማለት እንደፈለገ/ች እንዲያውቁ አያስቡ።

ETHIOPIA HUB

ያደርጉ	አያድርጉ
የሚፈልጓቸውን እውነታዎች ለማግኘት ጥያቄዎችዎን ይገድቡ። ለምሳሌ እንዲህ ይበሉ ፡ “ምንድን ነው የሆነው? መቼ ነው የሆነው? የት ነው የተከሰተው? ማን ነው ያደረገው? እንዴት ነው ያወቅካቸው/ያወቅሻቸው?” ነገሮች ወደሚቀጥለው ደረጃ ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ለማግኘት እነዚህ ጥያቄዎች በቂ ናቸው።	ቃል መግባት። የተነገርዎትን ለማንም እንደማይናገሩ በፍጹም ቃል አይግቡ። ይልቁንስ እንዲህ ይበሉ፡- “ይህን ስለነገርከኝ/ሽኝ አመሰግናለሁ” ከዚያ ቀጥሎ ምን እንደሚሆን እና ከማን ጋር መነጋገር እንዳለብዎት ለልጁ/ ለልጅቷ መንገርዎን ይቀጥሉ። በዚህ መንገድ ሕፃኑ የበለጠ ያምንዎታል/ታምንዎታለች እናም ቀጥሎ ምን እንደሚሆን መረዳት ይችላል/ትችላለች።
ሁልጊዜ መመዝገብን ያስታውሱ፤ ይህ ሕፃኑ/ኗ ቀደም ሲል የተነገረውን/ችውን እንዲደግም/እንድትደግም ከማድረግ እንዲቆጠቡ ይረዳዎታል።	

ከልጁ/ከልጅቷ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ እና የተናገረውን/የተናገረችውን ነገር ከመዘገቡ በኋላ ወዲያውኑ እርምጃ መውሰድ እና በድርጅትዎ ሪፖርት ሂደት መሠረት ሪፖርት ማድረግ ያስፈልግዎታል።

መሣርያዎች እና መርጃዎች

የሕፃናት ጥበቃ እና ጥበቃ
ሕፃናት አድን ድርጅት :

https://www.savethechildren.net/sites/www.savethechil-
dren.net/files/SCI_HR_POL_Child%20Safeguarding%20Exte
rnal%20Policy_EN.docx.pdf

የዩኒሴፍ የሕፃናት ጥበቃ :

https://www.unicef.org/protection

የኢትዮጵያ የመረጃ እና ድጋፍ ማዕከል፡ የሕፃናትን ደህንነት መጠበቅ - የጥበቃ መሠረታዊ ነገሮች

https://ethiopia.safeguardingsupporthub.org/sites/default/-
files/2020-12/KCS%20Standards%202%20Pager%20AK.pd
f

በኢትዮጵያ የጥበቃ መሠረታዊ መረጃ እዚህ ይመልከቱ :

https://ethiopia.safeguardingsupporthub.org/sites/default/-
files/2020-12/KCS%20Standards%202%20Pager%20AK.pd
f

በኢትዮጵያ አስተማማኝ ፕሮግራሞችን እንዴት መንደፍ እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት እዚህ ያንብቡ :

https://ethiopia.safeguardingsupporthub.org/sites/default/-
files/2020-12/RSH%20Safeguarding%20Journey%20Intro%
20Slides-compressed.pdf

ከልጆች ሪፖርቶችን እንዴት መቀበል እንደሚቻል

የልጅ እርዳታ፣ ይፋ ማውጣትን እንዴት እንደምናስተናግድ :

https://safeguardingsupporthub.org/multimedia/respond-
ing-re-
port-sexual-exploitation-abuse-or-sexual-harassment-nigeria

ጉዳዮችን ወደ ድጋፍ ሰጪ አካላት ማስተላለፍ

በኢትዮጵያ በትምህርት ቤት የፆታ ላይ ከተመሠረተ ጥቃት ምላሽ መስጠት ፡

https://www.unicef.org/ethiopia/media/1366/file/Addressing%20SRGBV%20in%20Ethiopia:%20A%20scoping%20study%20of%20policy%20and%20practice%20to%20reduce%20gender-based%20violence.pdf

የጉዳይ አያያዝ ፍሰት ፡

https://safeguardingsupporthub.org/multimedia/case-handling-flow-chart-nigeria

ስምምነት እና ምስጢራዊነት ፡
https://safeguardingsupporthub.org/multimedia/consent-and-confidentiality-nigeria

የልጆች ተሳትፎ
የሕፃናት አድን አሳታፊ የድርጊት መረጃ መሣሪያ ፡

https://resourcecentre.savethechildren.net/library/child-and-youth-friendly-participatory-action-research-toolkit

የሕፃናት አድን ትርጉም ላለው የሕፃናት ተሳትፎ መሠረታዊ መሥፈርቶች ፡

https://resourcecentre.savethechildren.net/library/nine-basic-requirements-meaningful-and-ethical-childrens-participation

የሕፃናት አድን የሕፃናትን ተሳትፎ በፕሮግራሞች ትንተና ፣ ዕቅድ እና ዲዛይን ላይ ፡

https://resourcecentre.savethechildren.net/library/childrens-participation-analysis-planning-and-design-programmes-guide-save-children-staff

ከልጆች ጋር የመግባባት መርሆች

የሕፃናት አድን ድርጅት መረጃ ማዕከል፡ ከልጆች ጋር መግባባት፡ ለመንከባከብ፣ ለማነሳሳት፣ ለማስደሰት፣ ለማስተማር እና ለመፈወስ መርሆዎች እና ልምዶች 2011፡

https://resourcecentre.savethechildren.net/library/communicating-children-principles-and-practices-nurture-inspire-excite-educate-and-heal

ስለ ጥቃት ከልጆች ጋር ማውራት

አሁን አቁም! የልጆች ወሲባዊ ጥቃት ወሰን፡

https://www.stopitnow.org/faq/the-scope-of-child-sexual-abuse-definition-and-fact-sheet

ስለ ልጅ ጥቃት ከልጆች ጋር ለመነጋገር ጠቃሚ ምክሮች፡

https://ovc.ojp.gov/sites/g/files/xyckuh226/files/pubs/helpseries/pdfs/CATipSheet.pdf

የኢትዮጵያ ከወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት መከላከል PSEA መመሪያዎች፡

https://ethiopia.safeguardingsupporthub.org/sites/default/files/2021-06/3.1.1_PSEA_IASC%20Six%20Core%20Principles_A5_English.pdf

ዩኒሴፍ፡ በልጆች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመፍታት የማኅበራዊ እና የባህርይ ለውጥ
https://www.unicef.org/media/97721/file

የጥቃት ምልክቶች በልጆች ላይ
አንድ ልጅ ጥቃት እንደደረሰበት/ባት እንዴት ማወቅ እንደሚቻል፡

https://www.stopitnow.org/sites/default/files//documents/files/warning_signs_child_behaviors_1.pdf

በዳዮችን/ጥቃት አድራሾችን እንዴት መለየት እንደሚቻል፡፡

https://www.rainn.org/articles/child-sexual-abuse

አካል ጉዳተኝነት እና አካታችነት
አካል ጉዳተኝነትን ያካተተ የልጆች ከጥቃት ጥበቃ መመሪያዎች፡

https://resourcecentre.savethechildren.net/node/19086/pdf/disability_inclusive_child_safeguarding_guidelines_able_child_africa_save_the_children_2021_-seah.pdf

ማኅበረሰብ ተኮር የቅሬታ ዘዴዎች

How to Design and Manage Community-based Complaints Mechanisms (CBCM) | Safeguarding Resource and Support Hub (safeguardingsupporthub.org)

በኢትዮጵያ የማሳወቂያ እና ማስተላለፊያ አገልግሎቶች

ሪፖርት ለማድረግ (በእርዳታ ዘርፍ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ በተመለከተ)	የዓለም የምግብ ድርጅት (WFP) የጥሪ ማእከል፡ 6063 ከመደወል እና 6065 ከፅሁፍ መልእክት	ከሰኞ እስከ ሀሙስ፡ 2:30 - 11:00 ዓርብ፡ 2:30 - 7:30	አማርኛ
የምክር ድጋፍ ለማግኘት	ሴታዊት አለኝታ የጥሪ ማዕከል፡ 6388	ከሰኞ እስከ ዓርብ፡ 3:00 - 6:00 8:00 - 11:00	አማርኛ
የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት እና የምክር ድጋፍ ማግኘት	ዓለም አቀፍ የሜሪ ስቶፕስ የጥሪ ማዕከል፡ 8044	ከሰኞ እስከ ዓርብ፡ 3:00 - 6:00 8:00 - 11:00	ብዙ ቋንቋ ትግርኛን ጨምሮ

ማስታወሻ

ማስታወሻ

ስለ ሕፃናት ከጥቃት ጥበቃ ከልጆች ጋር ለመነጋገር

ETHIOPIA HUB

UKaid from the British people